5) የመሸጫ ማእከል በሌለባቸው አካባቢዎች ከመንግስት የግንባታ ፕሮጀክት የሚተርፈውን የሲሚንቶ ምርት ለሌሎች ገንቢዎች እንደቅደም ተከተላቸው የሚሰራጭበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ያሳውቃል፤

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ

ይህንን መመሪያ በሚተላለፉ ላይ አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 10.የመተባበር ግዴታ

የዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሁሉም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 11.የተሻሩ መመሪያዎች እና አሰራሮች

"የሲሚንቶ አቅርቦትና ግብይት መመሪያ ቁጥር 23/2012 ዓ.ም" የሲሚንቶ ግብይትን የሚመለከቱት ሁሉም ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ቁጥር 908/2014 ተሽረዋል፡፡

### 12.መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ይህንን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

### 13.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 17/2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ

ሚኒስትር

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር